# እኔስ.... . ተናገርኳት !

ስምሽን አላስታውሰው፣ ደግሜ አልጥራበት፣
ስምሽ ነው ጠንቀኛው፣ የእድሜ ልክሽ ጠላት።
ደምሽ ተንጠፍጥፎ፣ ይድረቅ ለወዲያኛው፣
እሱ ነው ስሪትሽ ፣የዘርሽ መገኛው።
ማጠንሽም ይንጠፍ፣ ይምከን እንደ በቅሎ፣
እስከመቼ ድረስ፣ ስንቱን ጉድ አብቅሎ።

አንጀትሽ ተፈትቶ፣ ይበተን ከሜዳው፣
ከሆድሽ መሽጎ፣ ዘር አሚያጋምደው።
ልብሽን ሰንጥቀው፣ ይዩብሽ ጉድሽን፣
መውደድ ጥላቻሽን፣ ሐዘን ደስታሽን።
ያየር ከረጢትሽ፣ ትንፋሰሽ ይቋረጥ፣
ነፍስ እያቋደሰ፣ ትውልዱን ከሚያስምጥ።

ክንድሽንም አጥፈው፣ ከደረት ይሰሩት፣
ሁሉን እያቀፈ፣............ .
ስንቱን ከሚያዋትት፣ ስንቱን ከሚያሟግት።
እግርሽ ሽባ ይሁን፣.........
እርሻ አትሂጅበት ፣ ውሀም አትቅጅበት፣
ቃርሚያ እየሰበሰብሽ፣ ግርድ አታመርቺበት።

ስስት እማያውቀው፣ ይታሰር አንጀትሽ፣
ፈትፋችና አጉራሹ፣ ጣትሽ ነው ደመኛሽ።
የናትነት ኅዳሽ፣ ሴትነትሽ ይክዳሽ፣
ሴት በመሆንሽ ነው፣ የሚያንከራትትሽ።
ጆሮችሽ ይንተቡ፣ መስማት ያቅታቸው፣
ውርደትሽን መስማቱ፣ ላይ እንባ ቀለብ ነው።

አይንሽን ሾርበው፣ ይጋርዱት በሽማ፣
ምን ያደርግለታል፣ መብቱን ለተቀማ።
መቀነትሽን ፈትተው፣ ያጥልቁልሽ ሱሪ፣
አሳብ ነው ልጅ መውለድ፣ አንቺ ድሃ ! አዳሪ።
እኔም እናቴ አልበል፣ አንቺም ልጄ አትበይኝ፣
ወፍዘራሽ ማንዘራሽ፣ የቲም ልጅ ከሆንኩኝ።

ቀብሬን ይማሱና፣ መርዶየን ይንገሩሽ፣
አንቺም አታልቅሽ፣ እኔም ባይኔ አልይሽ።
የኔን ነገር ለሷ፣ ተዋት አትንገሯት፣
ወለደችኝ እንጅ፣ እኔ መች ወለድኳት።
የልቤ እንባ ፈሶ፣ አንጀቴን አራሰው፣
መውለድ ምን ያደርጋል፣ ልጅ እዩከዳው ሰው፣

መውለድ ክብር ሁኖ ፣ ወግ ማረግ ካልታዬ
በካር ምን መቅኖ አላት፣.........
ቤቷ ከደኸዬ፣ ሽሏ ከጎፈዬ፣ ክብሯ  ከጠኸዬ ! ! !

አክሊሉ ሃይሉ
ከፍራንክፈርት - (ጃንዋሪ - 2012)

EthioLion.Com